# *የወደፊቱን በጋራ መገንባት፡ የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ስልታዊ ዕቅድ ማውጣት*

## *የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ምንድን ነው?*

የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ጤናማ፣ አስተማማኝ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እንዲሁም ከስርአታዊ ዘረኝነት የጸዳ ፍትሃዊ እና ትክክለኛ ማህበረሰብ ራዕይ ላይ ይሰራል፡፡ የመምሪያው ተልእኮ እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል ጤናማ፣ አስተማማኝ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ከጥቁር፣ ከሃገሪቱ ተወላጆች፣ እንዲሁም የተለያየ ቀለም ካላቸው ሰዎች ጋር በህብረት ለጋራ ጥቅም የሚያስፈልጉትን ሀብቶች እና ዕድሎችን መፍጠር ነው፡፡

## የሰብአዊ አገልግሎቶች ስልታዊ ዕቅድ ምንድን ነው?

የሰብአዊ አገልግሎቶች ስልታዊ ዕቅድ የመምሪያውን ተልዕኮ፣ ግቦች እና አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ የማድረስ ስልቶችን የሚገልጽ አጠቃላይ ዝርዝር ሰነድ ነው፡፡

ከጤና፣ ከማህበራዊ ደህንነት እና ከኢኮኖሚያዊ መረጋጋት ጋር የተተያያዙ ውስብስብ እና በየጊዜው የሚቀያየሩ ፍላጎቶችን ለመፍታት እንደ ፍኖተ ካርታ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣ በዚህም ስልጣኑ ነዋሪዎቹን ለመደገፍ ምላሽ ሰጪ እና ውጤታማ ሆኖ እንደሚቀጥል ያረጋግጣል፡፡

## የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ስልታዊ ዕቅድ መፍጠር ለምን አስፈለገው?

የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ የዲፓርትመንቱን ራዕይ እና ተልእኮ ለማሳካት ስልታዊ ዕቅድ እየፈጠረ ነው፡፡ ዕቅዱ ልዩነቶችን ለመፍታት ግልጽ የሆኑ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እና ተጓዳኝ እርምጃዎችን በማዘጋጀት ፍትሃዊ እና ትክክለኛ ማህበረሰብ የመፍጠር ጥረቶችን ይመራል፡፡ ፖሊሲዎች እና አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ ባህላዊ ሚስጥራዊነታቸውን እንዲሁም ለእያንዳንዱ ተደራሽነታቸውን በማረጋገጥ፣ ስልታዊ ዕቅዱ የመምሪያውን ተልእኮ የማህበረሰቡን ፍላጎቶች ለሟሟላት ከተነደፉ ልዩ ተነሳሽነቶች ጋር ለማጣጣም እና በጤና፣ በደህንነት፣ እና በኢኮኖሚያዊ ደህንነት ላይ ያሉ ስርአታዊ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ ይረዳል፡፡ እንዲሁም ለመምሪያው ሊለኩ የሚችሉ ግቦችን በማስቀመጥ እና እያንዳንዱ ነዋሪ የዘር ኢፍትሃዊነት ሳይጋፈጥ ሊያድግ ወደሚችልበት ማህበረሰብ ውስጥ ሂደቱን በመከታተል ተጠያቂነትን ያበረታታል፡፡

## የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ስልታዊ ዕቅድ ውስጥ ምን ውጤቶች ይታያሉ?

[የአርሊንግተን አውርጃ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ስልታዊ እቅድ በአካላዊ እና ስነምግባር ጤና ላይ ባሉ ውጤቶች ያተኩራል፤ እነዚህም የመኖሪያ ቤት መረጋጋት፣ ደህንነት፣ መከላከል እና ደህንነት፣ የኢኮኖሚ ደህንነት፣ አካታች የማህበረሰብ ግንኙነቶች፣እና ድርጅታዊ አቅም፡፡]

ለበለጠ መረጃ (https://arlingtonva.us/Government/Departments/DHS/Strategic-Plan) ይመልከቱ።

## የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የስትራቴጂክ ፍላጎቶች የዳሰሳ ጥናት ለምን ያካሂዳል?

የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የአርሊንግተን አውራጃ ነዋሪዎችን ፍላጎት ለመረዳት እና ለመለየት የሰብአዊ አገልግሎቶች ስልታዊ እቅድ ለማዘጋጀት የማህበረሰቡን አስተዋፅዖ ይፈልጋል።

**የዳሰሳ ጥናቱን ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

የዳሰሳ ጥናቱን ለማጠናቀቅ ከ10-15 ደቂቃ ይወስዳል።

**የዳሰሳ ጥናቱን የት ማግኘት እችላለሁ?**

የዳሰሳ ጥናቱን እዚህ https://www.research.net/r/ArlingtonCS ማግኘት ይችላሉ።

የዳሰሳ ጥናቱ በተለያዩ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ እና የማህበረሰብ አካባቢዎች እየተሰጠ ነው።

**የዳሰሳ ጥናቱ መቼ ይከናወናል?**

የዳሰሳ ጥናቱ እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 28 እስከ ታህሳስ 2/2024 ክፍት ይሆናል።

**በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ባለኝ ተሳትፎ ማንነቴ ያልታወቀ ነው?**

አዎ የዳሰሳ ጥናቱ የተነደፈው ሃቀኛ እና ትክክለኛ አስተያየትን ለማበረታታት ስም-አልባ እንዲሆን ነው። የእርስዎ ምላሾች በሚስጥር ይያዛሉ።

**የዳሰሳ ጥናቱ በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል?**

አዎ፣ ጥናቱ በእንግሊዝኛ እና በስድስት ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል፡- አረብኛ (عربي)፣ አማርኛ (አማርኛ)፣ ቤንጋሊ (বাংলা)፣ ሞንጎሊያኛ (Монгол)፣ ሩሲያኛ (Русский) እና ስፓኒሽ (Español)።

**የአርሊንግተን አውራጅ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ በዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች ምን ያደርጋል?**

የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት በአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ የሚሰጡ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለመረዳት እና ለማሻሻል እና ስልታዊ እቅድ ከማህበረሰቡ ፍላጎቶች ጋር ለማጣጣም ይጠቅማል።

**የዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች ወደፊት ለህዝብ ይቀርባሉ?**

ስለ አርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ መረጃ እና ተያያዥ መረጃዎች በ https://arlingtonva.us/Government/Departments/DHS/Strategic-Plan ላይ ይገኛሉ።

**ለተጨማሪ መረጃ እና ድጋፍ ማንን ማግኘት እችላለሁ?**

ለተጨማሪ መረጃ እና ድጋፍ እባክዎትን የድጋፍ ቡድናችንን በ team@carrington-consulting.com ያግኙ፡፡

**ስለ የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ስልታዊ ዕቅድ ተጨማሪ መረጃ እና የዚህ ተንሳሽነት ሂደት ምን እንደሆነ ለማወቅ ተጨማሪ መረጃ የት አገኛለሁ?**

ስለ የአርሊንግተን አውራጃ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ስልታዊ ዕቅድ ተጨማሪ መረጃ *https://arlingtonva.us/Government/Departments/DHS/Strategic-Plan* ላይ ያገኛሉ፡፡